# በኢትዮጵያ የምግብና የመድኃኒት ባለሥልጣን የተዘጋጀ

## ኮሮና ቫይረስ _ 19 በተመለከተ በተደጋጋሚ *ከህብረተሰቡ* ለሚነሱ ጥያቄዎች መልሶች

**ዓላማ፡-** የኢትዮጵያ የምግብና የመድኃኒት ባለሥልጣን የኮሮና ቫይረስ በሽታን ለመከላከል በሚደረገው ጥረት የጤና አገልግሎት ግብዓቶች እጥረት እንዳይፈጠር፤ ደህንነታቸውና ጥራታቸውን የጠበቁ ሕጋዊ ምርቶች ለጤና ባለሙያዎችና ለህብረተሰቡ መረጃ በፍጥነት ሳይቆራረጥ እንዲደርሱ ለማድረግ ነው፡፡

**ማሳሰቢያ፡-** ይህ ሰነድ **የኮሮና ቫይረስ** _ 19 መከላከያ ቁሳቁሶችን ሕጋዊ አመራረት፣ አሠረጫጨትና አጠቃቀም በተመለከተ ለአገልግሎት ሰጪ ተቋማትና ለህብረተሰቡ ለመስጠት ሲሆን **የኮሮና ቫይረስ** _ 19 መሠረታዊ የመከላከያ መንገዶችን የማይተካ መሆኑንና መረጃውም በየጊዜው የሚሻሻል እንደሆነ እንገልጻለን፡፡

**ጥያቄ/ የኮሮና ቫይረስ** _ 19 በሽታ ምን ዓይነት በሽታ ነው?

**መልስ/ የኮሮና ቫይረስ** _ 19 በሽታ በቅርብ ጊዜ በተገኘ ኮሮና ቫይረስ ተብሎ በሚጠራ ቫይረስ ምክንያት የሚመጣ ተላላፊ በሽታ ነው።

**ጥያቄ/ የኮሮና ቫይረስ** _ 19 በሽታ ክትባት ወይም መድኃኒት አለው?

**መልስ/** እስከ አሁን ድረስ ለዚህ በሽታ መከላከያ ክትባትም ሆነ መፈወሻ መድኃኒት የለውም፡፡ ሆኖም ተመራማሪዎች ለበሽታው መከላከያ የሚሆን ክትባትና መፈወሻ መድኃኒት ለማግኘት ሌት ከቀን እየሠሩ ሲሆን ውጤት ተገኝቶ አገልግሎት ላይ ለማዋል ብዙ ወራቶችን ስለሚጠይቅ አሁንም መንግሥት እና የጤና ባለሙያዎች የሚነግሩንን ምክር ተቀብለን ተግባራዊ ማድረግ አማራጭ የሌለው አማራጭ ነው፡፡

**ጥያቄ/ የኮሮና ቫይረስ** _ 19 በሽታን መከላከል ይቻላል? እንዴት?

**መልስ/** የሚከተሉትን በጥንቃቄ በመፈጸም አዎ ይቻላል፡፡

1) እጅን በውሀና በሳሙና ቶሎ ቶሎ በአግባቡ መታጠብ፣ ውሀና ሳሙና በአካባቢያችን ከሌለ ደግሞ የእጅ ማጽጃ ኬሚካሎችን (Hand sanitizer) በመጠቀም እጅን በደንብ ማጽዳት

2) አለመጨባበጥ

3) አካላዊ ርቀትን መጠበቅ (ቢያንስ 2 የአዋቂ እርምጃ ወይንም 2 ሜትር ርቀት ጠብቀው መንቀሳቀስ)

**ጥያቄ**/ የፊት መሸፈኛ ጭንብሎች **የኮሮና ቫይረስ** _ 19 በሽታን ይከላከላሉ?

**መልስ**/ በአሁኑ ወቅት **ከኮሮና ቫይረስ** _ 19 በሽታ መከሰት ጋር ተያይዞ የተለያዩ ሀገራትና ብዙኃን መገናኛ የፊት መሸፈኛ ጭንብሎችን አስመልክቶ የተለያዩ መረጃዎችን እያወጡ ይገኛሉ፡፡ ይህንን ተከትሎ በሀገራችን **የኮሮና ቫይረስ** _ 19 በሽታ ከተከሰተበት ጊዜ አንስቶ ዜጎች የተለያዩ የፊት መሸፈኛ ጭንብሎችን ሲጠቀሙ ይታያል፡፡ ይሁንጂ ከበሽታው አደገኛነት ጋር ተያይዞ ስለምንጠቀምባቸው የፊት መሸፈኛ ጭንብሎች ምንነት፣ ከምን እንደተሠሩ፣ የት እንደተሠሩ፣ አግባብ ያለው የመንግስት አካል ዕውቅና እንደሰጠው ማረጋገጥ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡የፊት መሸፈኛ ጭንብል መጠቀም ብቻ በቫይረሱ ከመያዝም ሆነ ከማስተላለፍ ሙሉ በሙሉ ስለማይከላከል ሌሎቹን የመከላከያ መንገዶች ማለትም እጅን ቶሎ ቶሎ በአግባቡ መታጠብ፣ አልኮል ያለው ሳኒታይዘር መጠቀም፣ አካላዊ ርቀት መጠበቅና ባለመጨባበጥ መከላከል ይቻላል፡፡

የተለያዩ የፊት መሸፈኛ ጭንብሎች በገበያ ላይ የሚገኙ ሲሆን **የኮሮና ቫይረስ** _ 19 በሽታን የመከላከል አቅማቸው ግን በሚሰሩበት የጥሬ ዕቃ፣ አዘገጃጀትና አጠቃቀም ይወሰናል፡፡

የፊት መሸፈኛ ጭንብሎች ዓይነቶች:-

1) ከጨርቅ የተሰራ **የፊት መሸፈኛ** ጭንብል (ማስክ)(**cloth masks**)፡- በቤት ውስጥና በፋብሪካ ከመቶ ፐርሰንት(100%) ጥጥ ወይንም ተመጣጣኝ ደረጃ ካላቸው የጨርቅ ዓይነቶች የሚመረቱ የፊት መሸፈኛ ጭንብሎች ለሕክምና አገልግሎት የሚውል የፊት መሸፈኛ ጭንብሎች የማይመደቡ ሲሆን የት እና ማን እነዚህን ዓይነት ጭንብሎችን ይጠቀም የሚለውን የጤና ሚኒስቴር የሚሰጠውን መግለጫና መመሪያ መከተል ያስፈልጋል ፡፡

2) **ለህክምና አገልግሎት የሚውል የፊት መሸፈኛ ጭንብል** (Medical mask):- ይህ ዓይነቱ የፊት መሸፈኛ ጭንብል ከሕክምና የፊት መሸፈኛ ጭንብሎች የሚመደብ ሲሆን ጭንብሉን ከለበሰ ***ታማሚ*** ሰው አፍ የሚወጡ ከፍ ከፍ ያሉ ቅንጣቶችን (large particles) አካባቢን እንዳይበክል ያግዛል፡፡ እንዲሁም ከፍ ከፍ ካሉ የደምና የሰውነት ፈሳሽ ፊዚካል ባሪዬር (physical barrier) በመሆን የጠብታ ብናኝ (droplets) አካባቢን እንዳይበክል ይከላከላል፡፡ በመሆኑም እነዚህን ዓይነት ጭንብሎችን መጠቀም የሚመከር ሲሆን ነገር ግን በዓለም አቀፍና አገር አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ እጥረት ስላለ ቅድሚያ የጤና ባለሙያዎች እንዲጠቀሙ ዕድሉን ብንሰጣቸው ጥሩ ነው፡፡ ***የእነዚህን ጭንብሎች ደህንነትና ጥራት የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን ፈቃድና ዕውቅና የሚሰጣቸው ሲሆን በሕጋዊ አምራች የተመረቱ ወይንም በሕጋዊ አስምጪ ወደ ሀገር ስለመግባታችው ይህንን በመጫን*** http://www.fmhaca.gov.et/covid19-publications/ ***ማረጋገጥና መጠቀም ይኖርበዎታል ፡፡***

3) **N95** የመተንፈሻ የሕክምና ጭንብል (**Surgical N95 respirator**):- ይህ ዓይነቱ የፊት መሸፈኛ ጭንብል ከሕክምና የፊት መሸፈኛ ጭንብሎች የሚመደብ ሲሆን የመደበኛ የሕክምና ጭንብልና የ**N95** መተንፈሻ ጭንብልን ጥምር ጥቅም ያለው ሲሆን በአካላዊ ከለላ (physical barrier) ከደምና የተለያዩ የሰውነት ጥቃቅን የጠብታ ብናኞችን በሳል ከአፍ የሚወጡትን እርጥበት ጨምሮ መከለካላል የሚያስችል ሲሆን በበሽታው የተጠቁ ታካሚዎችን የሚንከባከቡ የጤና ባለሙያዎች ብቻ እንዲጠቀሙበት ይመከራል፡፡ ***የእነዚህን ጭንብሎች ደህንነትና ጥራት የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን ፈቃድና ዕውቅና የሚሰጣቸው ሲሆን በሕጋዊ አምራች የተመረቱ ወይንም በሕጋዊ አስመጪ ወደ ሀገር ስለመግባታችው ይህንን በመጫን*** http://www.fmhaca.gov.et/covid19-publications/ ***ማረጋገጥና መጠቀም ይኖርበዎታል ፡፡***

**ጥያቄ/ የእጅ ማጽጃ** (Hand sanitizer) ምንድነው?

**መልስ**/ የእጅ ማጽጃ (Hand sanitizer) ማለት ተላላፊ የሆኑ በሽታ አምጪ ተሕዋስያንን ለመከላከል የሚረዳ ሲሆን ከአልኮልና ከሌሎች ንጥረ ነገር በፈሳሽ ወይንም በቅባት መልክ የሚዘጋጅ ነው፡፡

**ጥያቄ**/ የኮሮና ቫይረስ በሽታን ለመከላከል ምን ዓይነት **የእጅ ማጽጃ** (Hand sanitizer) ልጠቀም?

**መልስ**/ ማንኛውም በሕጋዊ መንገድ የተመረተ ወይንም ወደ ሀገር ውስጥ የገባ የእጅ ማጽጃ (Hand sanitizer) የአልኮል መጠኑ ቢያንስ 80 በመቶ (80%) እና ከዚያ በላይ ከሆነ ተላላፊ የሆኑ በሽታ አምጪ ተሕዋስያንን መከላከል አቅም ያለው ስለሆነ መጠቀም ይቻላል፡፡

**ጥያቄ/ የእጅ ማጽጃ** (Hand Sanitizer) ስገዛ ምን ማየት አለብኝ?

**መልስ**/ የአመረተው ድርጅት ስምና አድራሻ፣ የምርቱ መለያ ቁጥር ( batch number)፣ የአልኮል መጠኑ ከሰማኒያ በመቶ (80%) በታች አለመሆኑንና አገልግሎቱ የሚያበቃበት ወርና ዓመት መገለጻቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

**ጥያቄ**/ ከጨርቅ የተሠራ  የፊት መሸፈኛ ጭንብል ከኮሮና ቫይረስ ራሴን ለመጠበቅ ይረዳኛል?

**መልስ**/ የኮሮና ቫይረስ በሽታ አምጪ ተሕዋስያን በዓይን የማይታዩ በጣም ረቂቅ ስለሆኑ በቤት ውስጥ ከጨርቅ የሚዘጋጁ የፊት ጭንብሎች በበሽታው ከተያዘ ሰው የሚወጡ በቫይረሱ የተበከሉ የእርጥበት ቅንጣቶችን መከላከል እንደማያስችሉ የተለያዩ ተመራማሪዎች ይገልጻሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ሀገራት እነዚህን ከጨርቅ የተሠሩ የፊት ጭንብሎች በማህበረሰቡ ቢደረጉ የበሽታውን ሥርጭት ለመቀነስ ስለሚረዳ ህብረተሰቡ አካላዊ ርቀትን ከመጠበቅ ጎን ለጎን ሰዎች በሚበዙበት ቦታዎች ጭምብል ቢጠቀሙ ቫይረሱ እያለባቸው የህመም ምልክት  ካልታየባቸው ወደ ጤናኛ የቫይረሱን መተላለፍ ሊቀንስ እንደሚችል ይጠቁማል፡፡ የሀገራችን የጤና ሚኒስቴርም ህብረተሰቡ አካላዊ ርቀትን ከመጠበቅ ጎን ለጎን ሰዎች በሚበዙባቸው ቦታዎች የፊት መሸፈኛ ጭምብል እንዲጠቀሙ እየመከረ ይገኛል፡፡

**ጥያቄ**/ ሕጋዊ የእጅ ማጽጃ ኬሚካል(Hand sanitizer) አምራቾችና አስመጪዎችን እንዴት ማወቅ እችላለሁ?

**መልስ**/ የእጅ ማጽጃ ኬሚካል (Hand sanitizer) አምራቾችና አስመጪዎችን እውቅና እንዲሰጥ በሕግ ሥልጣን የተሰጠው ለ***ኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን*** ሲሆን ብቃታቸውን አረጋግጦ እንዲያመርቱ ወይንም እንዲያስመጡ ፈቃድ የሰጣቸውን ተቋማትና የምርቱን ስም ይህንን http://www.fmhaca.gov.et/covid19-publications/ በመጫን ይመልከቱ፡

**ጥያቄ**/ **ሕጋዊ ለሕክምና አገልግሎት የሚውል የፊት መሸፈኛ ጭምብል** (Medical mask) እና **N95 የመተንፈሻ የሕክምና ጭንብል** (**Surgical N95 respirator**) አምራቾችና አስመጪዎችን እንዴት ማወቅ እችላለሁ?

**መልስ**/ **ለሕክምና አገልግሎት የሚውል የፊት መሸፈኛ ጭምብል** (Medical mask) እና **N95 የመተንፈሻ የሕክምና ጭንብል** (**Surgical N95 respirator**) አምራቾችና አስመጪዎችን እውቅና እንዲሰጥ በሕግ ሥልጣን የተሰጠው ለ***ኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን*** ሲሆን ብቃታቸውን አረጋግጦ እንዲያመርቱ ወይንም እንዲያስመጡ ፈቃድ የሰጣቸውን ተቋማትና የምርቱን ስም ይህንን http://www.fmhaca.gov.et/covid19-publications/ በመጫን ይመልከቱ፡

**ጥያቄ**/ ከኮሮና ቫይረስ በሽታ መከላከያ ምርቶች ጥራትና ደህንነት ጋር ችግር ቢያገጥመኝ ወይንም ደግሞ ባይ ለማን ማሳወቅ አለብኝ?

**መልስ**/ እነዚህን ስልክ ቁጥሮች በመጠቀም ወይንም በዚህ ኢሜል 8482 ወይም +251-11-552-41-22 etcovid19@efda.gov.et መላክ ይችላሉ፡፡